## ምዕራፍ ፱ ከፋ እጅ ።

### መ ግ ለ ጫ ።

በቡናና በዝባድ ንግድ ከጠቅላይ ግዛቶች (ውስጥ) ሁሉ በፊት የታወቀ ከፋ ነው ። በዐሥራ አንደኛው መቶ ዘመን ቡናን መጠጣት የጀመሩ አቦል ቶና በረካ የሚባሉ የከፋ ሰዎች ናቸው ። መሬቱ ለምለም ዛፉ እረጃጅም ነው ። ቡን ኮረሪማ ዝንጅብል አና ናስ በየዱሩ ወፍ አራሽ ይበቅላል ። ባመት ፫ ጊዜ ሊዘመር ይችላል በሊሙ ውስጥ የሚገኘው ቀርቀኅ እንደበርሜል ጠላ ያስጠምቃል ። ብዙ መዋቶች ይገኙበታል ።

በአዋ በረሃ ማነኛቸውም የዱር አውሬ ይገኝበታል ሕዝቡ በተግባረ እድ በጣም የገፋ ነው ። በጅሬን ከተማ ብዙ ጥንታዊ ጥበብ ይሠራበት ነበር ።

ዋና ከተማው ጂማ ነው ።

አውራጃዎች ሀ) ጂማ ፡ ለ) ከፋ ፡ ሐ) ማጅና ጐልድያ ፡ መ) ኵሎና ኮንታ ፡ ሠ) ጊሚ ራ ናቸው ።

ወንዞች ፡ ጊቤ ፡ ጐጀብ ፡ አሞ ፡ ጂንቻ አረንጋ ናቸው ።

ወሰን በሰሜን ከወለጋና ከኢሉባቦር ፡ በምዕራብ ከሱዳን ፡ በደቡብ ከኬንያ ፡ በም ሥራቅ ከጐሙ ጎፋና ከሲዳሞ ከአሩሲና ከሸዋ ጋራ ይዋሰናል ።

ል ብ ድልብ የጨበትሽበት እጅሽ ምድረ ከፋ
አስተውሎ ላየው እንደምን ይሰፋ ።
ቡናውን ዝባዱን የዘገንሽበት
ከሙንና አናናስ የምትተክዪበት
ብሩንና ወርቁን የምታፍሺበት
ዕንቍና ጌጣጌጥ የምትሠሪበት
የጥንቱን መሣሪያ ምታነጥሪበት
አንድም ማይቸግረው ባለሙሉ ሀብት
ከፋ እጅሽን መሳይ የት አለ አካላት ።
ያ ረጃጅሙ ዛፍ እጅግ የሚያምረው
ስጋጃውም ሣርሽ ምንጣፍ ሚመስለው
ሕሊና ማራኪ የጅሽ ሐረግ ነው ።
ቀረሮ አውራ ጣትሽ ስመ ነፍጠኛው
አልፎ ሃጁ ልቤን ወጥሮ ያዘው ።
ረጃጅም ዋርካ ትልቁ ጣትሽ
የቀለበት ጣት መቃው ቅርቃኅሽ ።
ያ ታናሹ ጣትሽ ለምለሙ ውልክፋ
በጣም ደነደነ ዝግባ መስሎ ሰፋ
ይህ ሁላ ልምላሜ አጥቅሽ የወጣው

ከጅሽ በበቀለው ከጣትሽ ላይ ነው ።
የእጅሽን ልምላሜ የእጅሽን ውበት
ይገርመኝ ነበረ እመ! ሲያወሩት ።
እኔም ስቅለበለብ በቀደም መጥቼ
በጣሙን ደነቀኝ ማማሩን ዐይቼ ።
ያ ሀብታም ከፋ ሰው ሁሉን የጨበጠ
እንደ ናት ለስላሳ በቅባት ያጌጠ ።
ደግሞም ከዚህ በላይ እጅግ ገዳም ነሽ
ዕድልሽን ይነግራል ሐረግ መንገድሽ ።
፪ ዐይቼ ሲገርመኝ ልስላሴውን
ደግሞውንም ሞክሬ አጨባበጡን ።
ተክሉና ውበቱ ልቤን ማረከው
የጥርኝሽ ዝባድ ሽታው ዝነኛው
ልምላሜው ቅባቱ አንቺ የተቀባሽው
ዐወደው አንጐሌን ቀልቤንም መሰጠው ።
እጅና እግሬን አሥሮ ሠውሮ አቲቴን
ናላዬን አዙሮ አውሮት ዐይኔን
የፍጢኝ ጠፍሮ ገነዝ እንደ በድን
አድንቆት ቀበረኝ እረ እንዴት ልዳን ።
ማንም ሰው ቢመጣ በእጅሽ ከያዝሽው
ሀብትሽን እያየ ማምለጫም የለው ።
እጅሽን ያላየ በሩቅ ሲፎክር
አቅምሺው እንደኔ ይምስለው መንክር ።
ሲሳይሽን በልቶ እጅሽ ቢጥመው
ተማረከ በእጅሽ አልፎ ሃጁ ሰው
ዐይቶ መመርመሩን ደከመው ናላዬ
በእጅሽ የያዝሺውን ንገርኝ እማዬ

ልብ አንተም ባድናቆትህ ነካክተሽዋል
ግን እነግርሃለሁ የቀረውን ሁል ።
ና በል ተከተለኝ ሁሉን ላሳይህ
በቃሌ በወሬህ ግርር እንዳይልህ ።
ከፍክሬ ረብርቤ የተከልሁት ዱር
ባለም ካሉት ደኖች የለውም ወደር ።
ዕየው ልብ አድርገህ ያን ጫካ ከሩቅ
ማነው ሚደፍረኝ ባይ ዝሆን ሚደብቅ ።

አንበሳና ነብር ቀጭኔና ሳላ
በጐጀብ በራሃ አንድነት ሲበላ
ፀሐይ አያየውም በዛፎቹ ጥላ ።
፫ እስቲ ተመልከተው ያንን ትልቅ ዋርካ
ጥላው የሚሸፍን አጐማሱ ሚያረካ ።
እንዲሁም ቀረሮ የሰንበ ጓደኛ
ጥድና ዝግባንም የዕፀዋትን ዳኛ ።
ውልክፋ ግራዋ ገተም አዛምራ
ማኽሊዮ ያበቅላል የዕንጨቶችን አውራ ።
ታናናሹንማ ስንቱን ዐስቤው
እንዲያው በየደጁ ቤቱ ይቍጠረው ።
ባታየው አንጋጠህ የዛፎችን ጫፍ
እንዲያው እያዳፈስህ መሬቱን ስታልፍ
ሣሩ እከ ቀረልህ የምድር ምንጣፍ ።
የሚታየው ጒድር ልብን የሚያሳሳ
ስጋጃ ልበለው ወይንስ ወላንሳ ።
ሰምበሌጥ ችውችዋ አክርማና ሰርዶ
ይመስላል ለሚያየው የዱር አጋሚዶ ።
ደግሞም ከዚህ በላይ የመስኬ ልምላሜ
ያስንቃል ሳዱላ ያማራ ሴት ጋሜ ።
ምንም ጫካውን ሳይ ባልናገረው
ዛፉን ስመለከት ባለስተውለው
ልምላሜውንም ሳደንቅ ባለስተባቃው
ዐይኔን ሲሸፍነኝ ፊቴን ሲያለብሰው
ተሰማኝ ስርስሩ ገታም ጓደኛው ።
እንኳንስ እኔና የሌለው ዐይንም
ዳሶ ይረደዋል ሣርሽን ለምለም ።
አሁንም ዝም ብለሽ ሳታስበ፣ እኔን
አዳምጥሻለሁ ቀጥዪ ሥራሽን ።

**ኢትዮጵያ** በላ ተከተለኝ እንጐብኝ አዝመራ
ብጅማ በከፋ በሸዋ ጊሚራ
አለኝ ወሰው ሰብል ወገን የሚያኰራ
የክረምት ደመና ፀሐይ ማይቀደው
፬ ጀግጀግ ጨለማ ብርሃን ማይዘልቀው
ረጅም ተራራ ጉም የሸፈነው

መስሎ ያስፈራል የሊሙ ጫካው
የከፋና የማጅ የሸዋ ጊሚራ
ደናቸውን ብታይ ይገበሃል ግራ ።
ኩሎ ኮንታ ጂማ የሚገኘው ዱር
መከሊ ነው መከሊ ነው የለውም ወደር
የሊሙ ቅርቃን ሻንዳው ረጅም
ደግሞም በስፋቱ በጣም ወፈፍራም
ባለም ቢዞሩ አቻ የለውም ።
ሚበቅለው ቅርቃን በከፋ ጊሚራ
ይችላል ላፋቱ ያደራሹን ጣራ ።
ቅርንጫፉ ማገር ጠርብ አንጓው ሲሆን
ሻንዳው የውቃ መቅጃ ሽቆው ቤት ክዳን ።
ቅርቃኃው ጠርብ ነው ሽምበቆ ሳጋው
የሊሙን አድራሽ እኔ ስሠራው ።
ጐጀዬ ማማሩ ወዲያውም መቅለሉ
በሽምበቆ ቅልስ የተሠራው ሁሉ ።
ጥዴንም ባየሽው በገለብ በማጅ
በየር ቁመት የዎ ዓለምን ሲዋጅ።
በውፍረት በመጠን ስላልተካከሉ
ግቡ ገብሩ አለ ዕፀዋትን ሁሉ ።
በዱር ቤተ መንግሥት ተቀዳጅቶ ዘውድ
አስጠራው ሁሉንም በሰልፍ በረገድ ።
አምባሳደሮቹ ቀረሮና ሰምበ
ክቡራት ወይዛዝርት ዋንዛና ቅላበ
ዋርካ ጥቍር ዕንጨት ገተም መሳፍንቱ
አምጃና ችብኃ ደግሞ መኳንንቱ
ባሕር ዛፍ ምስለኔ ባላባት ግራር
ይላሆ ምሳና ያገር ወታደር
አገፋሪ ነፋስ ሲያስተናብራቸው
ቀርበው እጅ ነሡ ሁሉም በተራቸው ።
፫ መንግሥቱ ከጸና ካሆነ ሰላም
አንድነት ገበረ የዕፀዋት ዓለም
ስለዚህ ከቀኍጥር ቀረጥ አይገባም ።
መስፍኑ አቶ ዋርካ በጣም ቢለው ደስ
ሊአከብር አስበ ልምላሜውን ንግሥ

የዕፀዋትን ጌታ የታላቁን ጽድ
ልብስ ጥላ አለበሰው ዜጋውን ዐጸድ ።
ደግሞ አቶ ዋንዛ የበቃ የነቃ
ምድሩን አለበሰው ቅጠል ካባ ላንቃ ።
ይህ ሁሉ መሳፍንት ይህ ሉሉ ነገሥት
በእጄ ሚተዳደር እኔ የሾምሁት ።
ምን ይበላል ብለህ አንተ ብትጠይቀኝ
ለመልስ ዝግጁ ነኝ ዝም ብለህ አድምጠኝ ።
ዘለዓለም የምሰጥ ታላቅ ብልጽግና
በዓለም የታወቀ አለኝ ጥሩ ቡና ።
ቄፍሬ ኰትኳቼ እንኳን ዘርቸው
ወፍ አራሹ ጫካ ገበው ዳዋ ነው
ከሺህ ዘመን በፊት ጣዕሙን ሳላውቀው ።
እንዲጠፋ ዱሩ እንዲለማ አገሬ
አቃጥለው ነበር ቄርጬ መንጥሬ ።
ደረቁን ማገዶ ርጥቡን ማገር
አደርገው ነበረ ለቤቴ ትዳር ።
ከዕለታት አንድ ቀን በዱሬ ተጋን
እየዘራሁ በትጋት ዕፀው ስፈትን
መርምሬ አገኘሁት የቡና ጥቅሙን ።
በከፋ ጉልቻ በሊሙ ጀበና
አፍልቼ ስጠጣ የቀላውን ቡና ።
ኰርቼ ቁጭ ብዬ በጂማ ወምበር
አንጋጦ ጊሚራ ያደንቀኝ ነበር ።
ቡናን የቀመሱ በመጀመሪያው
ከልጆቼ ሁሉ እነዚህ ናቸው
ታናሹ በረካ ትልቁ አባ አቦል
በመካከላቸው ቶና ይመጣል ።
፮ ከዚህማ ወዲያ ቡናን ባፈላው
ሀገሬን በሞላ ሽታው ዐወደው ።
ዓለም ሲሮጥ መጣ ምን አገኘሽ ሊል
እንዴት ያለ ፍሬ ነው ምን መሳይ ቅጠል ።
ገና በሩቅ ሳሉ የሚያውድ ሽታው
ጣዕሙ ምን ይል ይሆን ለቀመሰው ሰው ።
ጣሙን የሚያፍታታ ድካም የሚያጠፋ

አእምሮ የሚከፍት አንጎል የሚያፋፋ
ከቶ ምን ይዘሻል በእጅሽ መሃል ካፋ ።
ጥበቡን ንገሪን እንዴት ሠራሽው
ስልቱን አስተምሪን በምን ዐወቅሽው ።
ዓለሙ በመላ ቢነዘንዘኝ
በእንማር ጥያቄ ቢቸከችከኝ
ዘዴዬን ገልጬ ስልቴን አስፋፍቼ
አሳየሁት ላለም አርሚ ኰትኳቼ
ቀዩን ለቃቅሚ በጀበና አፍልቼ
ናኘሁት ለሕዝቡ በፍንጃል ቀድቼ ።
ከዚያን ለት ጀምሮ ፍጥረት ቢወደው
በእጄ ማስተወሻ ቡናን ካፌ አለው ።
በፊት ተደሰተ የኔው አካላት
ደቡ ስለነቃ በቡና ሙቀት ።
በጣም ደስ እንዳለው ሰውነቴን ሁላ
ቢተርፈኝ ላክሁትኝ ላለሙ በመላ ።
መጀመሪያ ቀምሶ ጎረቤቴ ዐረብ
እጅግ ፈነጠዘ ደስ ብሎት ከልብ ።
ወዲያውም ላከለት ለግብጽ ጓደኛው
ለትልቁ እስያ ለባልንጀራው ።
የልብ ወዳጃችሁ ታማኝ ስለሆንሁ
የሚጣፍጥ ነገር ገዝቼ አመጣሁ
ሌት ተቀን ሳትረሡ በሱስ ልባችሁ
ቈልታችሁ ወቅጣችሁ ጠጡት አፍልታችሁ
ደጓን ኢትዮጵያን እያሰባችሁ
፪ እነሱም ዕለቱን አፍልተው ቀምሰው
ይጣፍጣል አሉ አንድነት ሁነው
በበነጋው ግን ለመተው ቢያስቡ
ወልፍ ሁኖ ተገኘ መዘዙ ስበቡ ።
ያለ እህል አይውሉ ምሳ አድርገውት
ራት ሊሆን አይችል ማታ ቢጠጡት ።
እረ እንዲያው በሽታው እያላቸው ውል
ሱስ ንጉሥን ሁኖ ይገዛቸዋል ።
ብልጽግና ሸቼ ለወርቅ ብሸጠው
ዐረብና እስያን ሁሉንም ገዛው ።

በግመል ተጭኖ በመላ ዐረብን
አንድ አርጎ ሲገዛ ለብዙ ዘመን
ሌላ አገር መኖሩን ስለሰማ ዜና
በመርከብ በግመል በበቅሎ ሆነና
አውሮጳን ወረረው አሰፋ ምስፍና
በምሥራቅም በኩል ደረሰ ከቻይና ።
ባለም ላይ ሰፈፈ ገዛ አሜሪካን
መጥተው ሰገዱለት ሕንድና ጃፓን ።
ፍጥረቱን በሙሉ ባሪያ አድርጎ ዐረፈ
በጉማሪ አለንጋ ወልፍ እየገረፈ ።

**ልብ** የቡናሽ ታሪኩ ረዥም ነው በጣም
በጽሕፈት ነው እንጂ በቃል አይወጣም ።
ሌላውን ንገሪኝ ለውጠሽ ወጉን ፤
ኮረሪማ እናናስ እንዳለሽ ከሙን ።

**ኢትዮጵያ** ይኸማ ምን ገዶ በጄ ያለ ነው
ቅመሜን በሞላ ስማ ልቍጥረው
ከሙን ዳዋ መስሎ አረም ሳይነካው
በዴሬ ይበቅላል ማንም ሳይዘራው
ሰብስቤ ጠፍሬ ይዤው ብቅ ብል
ባለሙ ገበያ በውድ ይሸጣል ።
ሀብቴ ስለበዛ ስላልተቸገርሁ
ከሙኑን ከዳዋ እቈጥረዋለሁ ።
፫ ያለፈው አለፈ ለመጭው ዓመት
ከሙን ተሰብስቦ ይሆናል ወረት ።
ምን ቢበለጽጉ ቢሆኑ ቱጃር
ስለማይጠገብ የዚህ ዓለም ክብር ።
በወረት ያደጉ በዙ መንግሥታት
ድልብ የሰበሰቡ የሞላቸው ሀብት ።
አታላዩን ገንዘብ ኋላፊውን ብር
ጠገብነም አላሉ ከምኞት በቀር ።
ብዙ አልማዝ ጥሬ ወርቅ ሰብስበው በሥራ
ያበድሩት ጀመር ከወለዱ ጋራ ።
እኔም እንደነሱ ለመብላት አራጣ
ከሙኔን ጫጭኜ እስቲ ገብያ ልውጣ ።

**ልብ** አበጀሽ እማዬ ዐወቅሽ ለኑሮሽ

ምንም ሀብታም ብትሆኝ የማይቸግርሽ
ደግ ሥራም አይደለ ገንዘብ መናቅሽ ።
ከበላሁ ከለብስሁ ካገኘሁ ሲሳይ
ገንዘብ አልፈልግም ይብቃኝ አትበይ ።
ብዙ ወረት ለእጅሽ ወርቅ እንድታመጪ
ቅመምሽን ሰብስበሽ በገብያ ሽጪ
ንብረትን ሰብስበሽ ጨብጭ በጅሽ
በጣም እንዲከብር እንዲሰጥ ልጅሽ ።

<u>ኢትዮጵያ</u>      አይዞህ ልጄ ልጄ በምክርህ አምናለሁ
ነገሩ አይገባኝ መሥራት ጀምሬ አለሁ ።
እስከዚህ ይብቃና የከሙኑ ወሬ
ላውራህ ሌላ ቅመም ወጉን አሳጥሬ
በብዛት በልማት ዓለም ያወቀው
አለኝ ኮረሪማ በዱር በጫካው
ወፍ አራሹ ዳዋ ገቦው ደን ነው
እሱን እህል ብሎ ማነው ሚዘራው ።
ይደሽልቅና በክረምት ዘመን
አድጦ ይጥላል መንገደኛውን
እሱንም እንዲሁ እንዳይቀር በመና
አንጫርረዋለሁ ገበያ አወጣና ።

<u>ል ብ</u>      ጠንክረሽ እማዬ ተግተሽ ከሠራሽ
በቶሎ ያከብራል ያሁኑ ሐሳብሽ ።

<u>፱) ኢትዮጵያ</u>      ለሁሉም ጊዜ አለው ብቻ ታገሠኝ
ሠርቼ ለፍቼ የምከብር ነኝ ።

<u>ል ብ</u>      ልጅሽን ፀውቃለሁ ሀብታም መሆኑን
ሲሳይ ማይቸግረው ለብዙ ዘመን
በመት ሁለት ጊዜ ሲችል ሊያዘምር
ለምን አልከበረም አልሆነም ቱጃር ።

<u>ኢትዮጵያ</u>      ለካ አታውቀውም ወይ ምክንያቱን በውኑ
በጣሙን ቀላል ነው ጥያቄህ ያሁኑ ።
በእጄ ሚተዳደር ልጄ የሚያርሰው
ብዙ መሬት አለኝ ወሰን የሌለው ።
ያበቅላል በመላ ረጃጅም ዛፍ
ነፍስ የሚተግን ጥላው ሚያሳርፍ ።
ቀፎ ከዛፍ ስቅሎ ማሩን ይበላል

ትንሽ ዝቅ ብሎ ቡና ይለቀማል ።
ደግሞም አጐንብሶ ቈፍሮ በዶማ
በቅርጫት ይዝቃል ብዙ ከረሪማ
ሦስት ዐይነት ሲሳይ ሰብስቦ ሳይለፋ
ሲዘፍን ይኖራል ቁጭ ብሎ በከፋ ።
የጥንት ፍልስፍና የቈየው ካባቱ
ሚበላ ካገኘ ምንድር ነው ልፋቱ ።
ይል ስለነበረ በሳቅ በጭዋታ
ያሳልፈው ነበር ጊዜውን በቧልታ ።
ኮረሪማ ቡና ከላይ ነጭ ማር
አንድ ዛፍ አይሰጥም በማንም ሀገር
እንደዚህ ከሆነ የዱሩ ሲሳይ
ጭፈራውን ትቶ ለምን ይሠቀይ ።

ልብ ምንም ልጅሽ ብሆን አንቺም ብትበልጪኝ
ሐሳቤን ልንገርሽ እመ አትቈጪኝ ።
አዳም አባታችን አምላክ ሲፈጥረው
ገነትን ሊሠራ ሊኰትኵት ነው ።
እሱ ግን ሰነፈ ትእዛዝ አፈረሰ
አምላክ ልሁን ብሎ ከገነት ፈለሰ ።
ዕፀ በለስ በልቶ አምላክ ቢቈጣው
በፊትህ ወዝ ብላ ብሎ ረገመው ።
አምላክነት ሲሻ ተግባሩን ጠልቶት
ምድረ ፋይድ ወረዶ ሞት ተፈርደበት
በደል አይደለም ወይ እንደዚሁም ሁላ
ያ ጐረምሳው ልጅሽ ተግባሩን ከጠላ ።
የማይሠራ አይብላ ሲለን ጳውሎስ
ልጅሽ ይመገባል ውሎ ሲያፋድስ ።
መፈጠሩን ዐይቶ ለታላቅ ተግባር
ስንፍናውን ትቶ ይረስ ይቈፍር ።

ኢትዮጵያ ሌት ተቀን ቢሠራ አንተ እንዳልኸው ሁል
ብዙ ወርቅ ሰብስቦ ያደልባል እህል ፤
ለነገ አትበሉ ስትለው ወንጌል
አይሆንበትም ወይ አበሳ በደል ።

ልብ ሀብት የሚያስወቅሰው ቢያመልከው ነው እንጅ
ቢሰጡት ያጸድቃል ያወጣል ወዳጅ ፤

ይኸን የሚያስረዳ ተረት አለልን
እስቲ እናስተውለው አንድነት ሁነን ።
“ገንዘብ ካለ
በሰማይ መንገድ አለ„
ለጊዜው ደረሰ ባይናችን ዐየን
ገንዘብ እየሰጠን በሰማይ በረርን
አሁንም ይኸ ልጅሽ መጠጣቱን ትቶ
ሌት ተቀን ቢሠራ መሬትሽን ተግቶ
ይበለጽግና በጣም ሲቶጅር
የሚያስተዳድረው ይቀጥራል አሽከር
የሚበላው ሲያገኝ ወንድሙ ድኃው
ይህ መልካሙ ሥራ ታላቅ ምጽዋት ነው

ኢትዮጵያ	አዎን አዎን ልጄ አንተ እንዳልኸውም
በገንዘብ ካሠራ አይወቀስም
ሲቀብረው ነው እንጂ ሲጨፍርበት
ሀብታም አይወቀስ በገንዘብ ብዛት
እኔም ፈርጃለሁ አንተ እንዳልኸው ሠርቶ
ሀገሩን ያበልጽግ ማውደልደሉን ትቶ ።

ልብ	ሀብትሽን እናውጋ ትተን ነገሩን፤
ንገሪኝ እማዬ በእጅሽ ያለውን

ኢትዮጵያ	ከከሙን ከቡና ከጐደሬ ሌላ
አለልህ አናናስ ጥሬው የሚበላ ።
የሚወዳደረው ከጥቢ ነጭ ማር
በጣዕሙ የሚያስንቅ ያለሙን ስኳር
ይበቅላል አናናስ በጫካ በዱር ።

፲፩	ቅጠሉና አካሉ እሬት ሲመስል
ጣዕሙን ያላወቀ አልፎት ይሄዳል ።
የቀመሰው ግና ቈርጦ በስለት
በጣም ይጐመጃል አናናስ አምሮት
ገና በሩቅ ሲያየው በጣም ተደስቶ ።
አፉን ምራቅ ሞላው እእምሮውን ስቶ

ልብ	ጥሩውን አናናስ ብታነግሽው
አሁን አሁን አለኝ ልቤን አማረው

ኢትዮጵያ	በኩሉ በኩንታ ያለኝ ጅንጅብል
እንኳንስ ለኔና ላለም ይበቃል ።

በኵሉ በኮንታ በከፋ በማጅ
ሚበቅለው ዝንጅብል ሰውን ሚያጐመጅ
አእምሮ ሚያጠፋ ልብን የሚያጃጅ
ሚበልጠው አይገኝ ሚመሳሰል እንጅ
የወጥ ማጣፈጫ ቅመም በያይነቱ
በሬውና ላሙ የቤት እንስሳቱ ።
በእጇ የማይገኝ ከቶ ምንድር ነው
ለሰው ጸጋ ብሎ አምላክ ከሠራው ።
በኰሎ በረሃ በኰንታ በረት
እስቲ ና ላሳይህ ጥሩ ጥሩ ከብት ።
በሮች ይገኛሉ በሊሙ በከፋ
ሻኛቸው ያበጠ ዳልጋቸው የሰፋ ።
ፈረስና በቅሎ በግና ፍየል
በከፋ ሻኃዬ ሲተም ይታያል ።
በጃንጀሮ ሜዳ ፈረሴ ሲበር
ይመስላል መኪና የምድር ባቡር ።
ይነፍሳል ይበራል ይቀድማል መኪና
የሚወዳደረው ሯጭ የለምና ።
ስንዴዩና ገብሴ የታወቀው እህል
አሽቶ ጐምርቶ በጣም ሲበስል
ዘመድ የሞተበት አልቃሽ ይመስላል ።
አንገቱን ሲደፋ አቈልቍሎ ሲያይ
ሲሰርቅ የተያዘ ሌባ አይመልም ወይ ።
በቆሎው ማሽላው እግሩ ሲያባትር
ራሱ ሲከብድ እግሩ ሲወፍር
በታ የተመቸው ይመስላል ግራር ።
አብቦና አፍርቶ ዳጉሣው ሲያፈራ
የዱር አጋሚዶ ግርማው የሚያስፈራ ።
፲፪ የሀገሬ ሳዱላ ያገሬን ጐፈሬ
የቤተ መንግሥቱን የጥንት ጋሻጃግሬ
ይመስላል ራሱ ቀርቦ ለሚያየው
ምን ይዘሃል ብሎ ለመረመረው ።
ባመት ፫ ጊዜ የምዘራበት
ምንም አይቸግረኝ ዝናም ዘለለት ።
በጅማ በሆሎ ጥጡን ባየኸው

ቡልኮ ሠርቼ ሳሞናድለው
እንሰትና ቋሬጮ ሳለልኝ ጐደሬ
ችግርም የለብኝ እኔስ በሀገሬ
በከፋ በጅማ በኰሎ በኰንታ
በማጅ በጊሚራ ማር ያማረኝ ለታ
ማልዳ ተነሥቼ ከሄድሁኝ ፍለጋ
ጠግቤ እመጣለሁ ሳለልኝ አማጋ ።
ደግሞም ከዚህ በላይ በሰፊው ካሰብሁ
ቀፎዬን ሠርቼ ዛፍ እወጣለሁ
ንብዋ ትገባና በትቂት ቀኖች
እስከፋ ነጭ ማር ትሞላዋለች ።
ካንድ ወር በኋላ ንቧን አራግፌ
እሄዳለሁ ቤቴን ነጭ ማሬን ጋፍፌ ።
አስቀምጬዉ ቢሆን ቀፎዬን በክብር
ጭቃ ይሆን ነበር ይህን ጊዜ ማር ።
ወለላው የበዛ ዝናው የተሰማ
አለልኝ በሊሙ ስመ ጥሩ ጣዝማ ።
ነቃቅሎ ይጥላል ከሥሩ በአንድ አፍታ
ማርና ጣዝማዬ የልብን በሽታ ።

ልብ　　እማዬ ንገሪኝ በሽቱ በኩል
ከቤትሽ እንዳለ አደስ የሥር ኩል ።

ኢትዮጵያ　　የማሳይህ ሽቱ በብዙው አለኝ
እሰይ እሰይ ልጄ እንኳ አሳሰብሽኝ
እሠራ ነበረ ሁሉን በያይነቱ
አደስና ስምቡል ልዩ ልዩ ሽቱ ።

፲፫ በየበረሃዬ አድኜ ጥርኝ
ለዝባድ ለሽቱ አረባለሁኝ ።
ልዩ ልዩ ምግብ ካቀረብሁላት
ተግታ ትበላለች ያላንዳች ዕረፍት ።
ትውጥ ትውጥና ስትወፍር በጣም
የሚወርደው ላቧ ዲካ የለውም ።
ብርድም እንዳይበርዳት ሌት ተቀን ተግቼ
አነዳለሁ እሳት እኔው ተጉልቼ ።
እንደዚህ ለፍቼ ማገኘው ዝባድ
ባለሙ ገበያ ይሸጣል በውድ ።

የጥርኝ መደብር መፈጠሪያውም
ከፋ ላይ ነበረ ከመላው ዓለም ።

<u>ልብ</u> ስለ ቤት እንስሳ ስማሁኝ ጥቂት
በዩ እሰቲ ንገሪኝ ከዱር አራዊት ።
ባየሁት በረሃ ባጠናሁትም ደን
የሚገኘው አውሬ የለውም ወሰን ።
በአሞ በረሃ በጐጀብ ጅረት
ነግሠው ይኖራሉ የዱር አራዊት ።
ዐፄ ዝሆን ነግሦ ሠራዊት ሲነግ
በሩቁ ያገሳል ነጋሪት አንበሳ ።
ነጋሪት አንበሳ በሩቅ ቢጐሰም
ሠራዊቱ ሁሉ ጀመረ ይተም ።
በድምፁ በግርማው ሲያዳምቅ ቀበሌ
ይመስላል ጉሬዛ ያገር ሽማግሌ ።
ጂምናስቲክ ሲሠራ በዛፍ ላይ ዝንጀሮ
ጠጣ ሲያቀነቅን በድምፁ ከበሮ
ከመሬት ይዘፍናል ተቀባይ ቀበሮ ።
በአሞ በረሃ ቃላቁ አዳራሽ
በሊሙ በረሃ ሰፊው እልፍኝሽ
ጐጀብን አንጥፈሽ ግቤን ጐዝጐዘሽ
ነምርና ደፋርሳ <u>ወረበና</u> ጐሽ
<u>ከርከሮ ማሻንብል</u> አንድነት ጠርተሽ
አራዊትን ሁሉ ትጋብዢአለሽ ።

<u>ኢትዮጵያ</u> ስላራዊት ይብቃ አንተ ያወራኸው
ከዚህ ሌላም የለኝ የምጨምረው ።
እንዲያው ሳንናገር ብዙ ዘለናል
የላስቲክን ሐረግ ከዕፀዋት በኩል ።
፲፬ በዱሬ ሚገኘው በጂማ በከፋ በማጅ በጊሚራ
ልጄ ጥቅሙን ዐውቆ ጠንክሮ ቢሠራ ።
ይችልለት ነበር የጐማውን ጣጣ
ብሩን ከሚደፋ ወርቁን ከሚያወጣ ።
ወተቱ ሲወጣ መግቻ የለውም
ግንዱ በጣም ወፍራም ነውና ለምለም ።
ሐረጉ በዱሩ ተስቦ ተስቦ
ሰው አያሳልፍም መንገዱን ተብትቦ ።

ደኑን እንተውና እንግባ መንደር
ስለ እጁ ጥበባት ለመነጋገር ።

ልብ — ስለ እደ ጥበብ ላውራህ ብትይኝ
አሁንስ እናቴ እጅግ ደስ አለኝ
ሲያወሩ ሰምቼ እጀ ብልህ ነው
እጐመጅ ነበረ መቼ እንደማየው ።

ኢትዮጵያ — ዝም ብለህ አድምጠኝ ጆሮህን ከፍተህ
ቁም ነገር ነውና የማፈስልህ ።
ከካላቴ ሁሁ እጀ ሥልጡን ነው
ምንም ነገር የለ እኔ ማልሠራው ።
በጓዳዬ ጅማ ብረታ ብረት
ይቀጠቀጥ ነበር በታላቅ ብልሃት ።
ነበረኝ መሣሪያ በብዙው አውራጃ
የብረት ማቅለጫ ያፈሩ ማንደጃ ።
በከቢሽ መዐድን በአሞ ምድጃ ።
ለሁሉም ና እንሂድ ቦንጋና ድሬን
በጥንቶች ከተማ እንድታይ ክብሬን ።
ብዙ ዕቃ ይገኛል ካባ ጅፋር ቤት
ድሮ የሠራሁት የመጣው ከጥንት ።
በጫንቃ ሚነገት ጐራዴ ጨምሬ
አፎት ውላጋውን እጅግ አሳምሬ
የወርቅ ጋሻ ሠራሁ ለንጉሥ ጋሻ ጃግሬ ።
ኮርቻና ልጓም ለፈረስ ለበቅሎ
ይሠራ ነበረ አንድነት ተካክሎ ።
የበውና ጦሩ አፋና ካራው
ያስገርም ነበረ በእጀ ስሠራው ።
ደንቀዝና ወምበር እኔ እንደፈለግሁ
ሽንኮር አልጋ ማዕቶት በልቤ ካሠብሁ
በሐረግ አስጊጬ እጠርበዋለሁ ።
ታላቁን ቀረፎ ቄርጬ በስል
አደርገዋለሁኝ ገንበና መንቀል
፲፭ ለልብስም ማኖሪያ ደባይ አገልግል ።
ለንጉሡ ዙፋን ለቤተ መንግሥት
ቆርጬ አሰናዳሁ መንበረ ዳዊት
መታጠቢያ እንዲሆን ለወንድመኳንንት

ለጅማ መሳፍንት ለከፋ ነገሥት
በክብር ለታወቁ ለሴት ወዛዝርት
ብዙ ውኃ የሚይዝ ገንዳ አደረግሁት ።
መላ ሰውነቱን ባረብ ለጉምሁና
ለዘመቻ ጊዜ ሠራሁት ቅምጫና ።
ለርጎ መፈትፈቻ ለወተት ማቅረቢያ
ጠረብሁት ገበቴ ለገንፎዬ መብያ
ጀበናም ሠራሁት የጠጅ ማንቈርቈርያ ።
ለቤቴም በር ነው ሣንቃና መድረሀ
እረ ስንቱን ስንቱን ስንቱን ልንገልሀ ።
ጥሩ ውበትና መልክ ያልሰጠሁት
አይገኝም ከቶ አንድም ከዕፀዋት
ኮሶ ነው ቀረሮ ሰምበ ነው ገተም
ዋንዛ ወይስ ችብኃ ታላቁ ጽድም
እጄን ያልቀመሰ አንድ ዛፍ የለም ።
ቈርጬ ጠርቤ ስሰጠው ረገድ
ልወዳደር ይላል ከነጭ ፅብነ በረድ
ባየኸው ቅርቃኃን በሊሙ በከፋ
የሰምበ ጓደኛ ከዋርካ ሲጋፋ
እሱን የመሰለ ከሄት ይገኛል
የጠላ መጥመቂያ ጋንና በርሚል ።
ቅርቃኃ ነበረ በሰው አገር ጣራ
በጣም ቢደነድን አረግሁት ውጋግራ
የኤርትራን ድማህ የከፋን ቀረሮ
ይመስላል በሩቁ ሲታይ ተገትሮ ።
የጠላ መጥመቂያ ዓለም ያውቀው
እንሥራና ቢዴ ጋኔም እሱ ነው ።
ጠላውን ለመጥመቅ አንተ ተሰናዳ
ጋነ ፈጅ ሳሌ ፈጅ የመሰለ ሻንዳ
ቅርቃኃ አመጣለሁ ሂጄ ከሸራዳ ።
ይህንም ብንተወው በሸክላ በኩል
ቢዴውና ጋኑ ብረት ይመስላል ።
ጀበናው ብርሌ ጉሽ ኮልባ ጥዋዩ
ከባሕር የመጣ ብርጩቆ ዋንጫዬ ።
የእንጀራ ምጣዴ የርጎዬ ወጭት

አፍላል በገ ፊጅ ታላላቁ ድስት
ቅባት የጠገበ ያስንቃል ወሊት ።
ዕይልኝ ቀሚሴን ጥበብ ኩታዬን
የፈተልሁት እኔ ድርና ማጉን
ሸማኔውም እኔ ማሽሞነሙነው
በጥሩ ሸማ ዕቃ የማሳምረው ።
ጠጉር አስመስዬ የሴቱን ኩፍያ
የምጐነጕነው የለውም አምሳያ ።
ለጅማ መሳፍንት ለእነ አባ ጅፋር
ለቤት መጋረጃ ላልጋው አጐበር
ለሰገነቱ ልብስ ለወንበሩ ክብር
ለመሬቱ ምንጣፍ ለባጡ ማገር
ባየኸኝ ስፈትል ጥሩ ነጭ ሐር ።
፲፮ እስቲ ተመልከተው አሸን ርባኑን
የወርቁን ጉትቻ የእጅ ቀለበቱን
የሴቱን መሣሪያ አልቦ ድሪውን
አንጥረኛይቱ እኔ የሠራሁትን ።
እስቲ ተመልከተው ትንሽ ብለህ ጠጋ
ይህን የወርቅ ጋሻ የሰፋን ውላጋ ።
ሾተሉን አፋውን ያንንም ጐራዴ
የምዋጋበትን ሲመጣ ወምበዴ።
ምሣርና ማጭድ ገለዶ መጥረቢያ
ማረሻና ወገል ጥሩ መቈፈሪያ ።
የመሬት ማረሻ የካንቻ መምቻዬ
ዕየው ተደርድሮ ይኸ መሣሪያዬ ።
ይህን ያየው ልጄም በጅማ ያደገ
ይሠራል መሣሪያ እየወለተገ ።
ጥበበኛው ጐበዝ ባጠናው ዕውቀት
ወርቅ ብር ቢያነጥር ቢያወጣ ብረት
ጥበብ ቢያሽሞነሙን ቢሠራ ብልኮ
አንቀልባ ቢያለፋ ደግሞም ጥሩ ደኮ ።
ላምነቱን ቢወጥር ጀንዲውን ቢፍቅ
መሣሪያ ቢሠራ ጉልህና ረቂቅ ።
የጠቢባን ጠቢብ ሀገር የሚጠቅም
አንት ባለእጅ ተብሎ አይሰደብም ።

ባገሬ በጅማ ደግሞም በጃንጀሮ
ራሱን የማይችል ሁሉን አጠናቅሮ
ቍጥሩ ሰውም አይደል ነው እንጂ ዝንጀሮ ።
ብረት ሠራተኛ ወርቅ ሠሪ ሸማኔ
አሁን የት ይገኛል ሚወዳደር ከኔ ።
የምታየው ዕቃ ልዩ ልዩ ዐይነት
ከውጭ የመጣ አንድም የለበት ።
ለከፋ ነገሥታት ለጅማ ሡልጣን
አሳምረው ነበር ዘውድና ጌጡን ።
በበሐ ጊዮርጊስ ኲቲ ሚካኤል
ጥንታዊው መሣሪያ ጥንታዊው ባህል ።
ተክቦ ይገኛል ሁሉም አንድነት
ወደር የለሽ ዕቃ የአባቶች ጥሪት ።
በአንዳርቻ ተሰቅሎ ቸሩ መድኀኔ ዓለም
አዳነ ከጥፋት ቅርሳችንን አዳም ።
ዘመነ መሳፍንት ዘመነ ሹነኔ
አጥፍቶት ነበረ በሥቃይ ድያኔ ።
ጥንታዊውን ዓለም የአበውን ዕውቀት
ቸሩ መድኀኔ ዓለም እስኪያድንበት ፤
የጥበቤ ብዛት የዕውቀቴን መጠን
ዐይተህ ለመረዳት እንሂድ ጅሬን ።

ል ብ ዐየሁት እናቴ በጣም ገረመኝ
የሚወዳደረው ማንም አይገኝ ።
ሀብትሽን ጥበብሽን ሁሉን ዐየሁት
በተቻለኝ መጠን ደግሞ አጠናሁት
እማዬ ንገሪኝ ደግሞ እስቲ ጥቂት
ለጤና የሚሆን ያለሽን መዋት ።

፲፯ እንሻገር ከፋ ደቀያ እንድረስ
አለ ጥሩ መዋት ድውይ ሚፈውስ
ሦስት አራት ቀን እየተጠመቀ
ከዚያው ቁጭ ብሎ ከተጠነቀቀ
ተግቶ ከታጠበ ውኃውን ጠጥቶ
ያወጠዋል ትሉን ጕትቶ ጕትቶ ።
ቂጥኝና ችግኝ የያዘው ቍምጥና
ሕዝቡ ይፈወሳል ወርዶ ዳዲበና ።

በዳዲበና ውኃ አንቺ በጣድሽው
ዓለሙን ለቀቀው አድፍ በሽታው ።
በግቤ በረሃ በጉጀብ በኦሞ
አለኝ ብዙ መዋት ያልተጠራ ደሞ ።
መድኃኒት ቀምሜ ከዕንጨት ከቅጠል
ደዌ የሚፈውስ የሚያጠፋ ትል
አድነው ነበረ ዓለሙን በውል ።
ባሁኑ ዘመንም ታላቅ ሆስፒታል
በጅማ ከተማ ቁሞ ይሠራል ።
ስፋቱ ገነት ነው ጽዳቱ ፀሐይ
ሙት ይድንበታል እንኳንስ ድውይ ።
በጥሩው መድኃኒት ባማረው ነፋስ
ሕሙም ይፈወሳል ከበሩ ሲደርስ ።
እርሻ ምማርበት ማረም መኰትኰት
በሥራው የገራ አለኝ ትምህርት ቤት ።
ፈረንጁና ልጄ ተጣልተውብኝ
በቡና ኰትኰታ በቡና ችግኝ ።
፲፰ ፊተኛው ቈረጠው እንዲፋፋ ሲል
ኋለኛው አለፈው ብሎ ይነግላል ።
ልጄ የተከለው ከሁሉ በለጠ
የፈረንጁ ቡና ደርቆ ተመለጠ ።
ማፍራቱ ቀረና ደረቀ ረገፈ
መዘበቻ ሁኖ ለትውልድ አለፈ
ጠላት የሚያሳፍር ወገን የሚያኰራ
በዐየኸው የልጄን ለምለሞ ሲያፈራ

ል ብ — ልጅሽ ከበረታ ከቻለ ራሱን
ነጩ ይሂድና ይምራ ሥራውን

ኢትዮጵያ — ለዚህስ ግድ የለም እኔም አስቤያለሁ
ነጩን አባርሬ ልጄን እተካለሁ ።
በጥበብ በዘዴ በፍጹም ዕውቀት
አለው ብዙ መንጋ የሚያረባው ከበት ።
ደሮውም ያስንቃል በወፍር በቁመት
የፍየል ወጠጤ የበጉን ጠቦት ።
የዘራው እህልና ያረሰው አዝመራ
የተከለው አትክልት ጠንክሮ እየሠራ

ሰው አይጨርሰውም ካልሆነ ገፈራ ።
ይህ ሰፊ ማሳዬ የጅማ ከተማ
ብዙ ትምህርት ቤት አዝመራን አለማ።
ሲመላለስበት ቊጥር የለሽ ነጋዴ
የልቤ ሐሴት ነው ደስታም ለሆዴ ።
እንደተነገረው ቢቀድም ተረት
ያሰለቻል እንጂ ብዙ መተቸት
፲፱ ከቶ ምንድር አለ ባለም ላይ ጥሪት
በእጇ የማልሠራው በእጇ ያልያዝሁት ።

ልብ    እውነትሽ እማዬ ታላቅ ሀብታም ነሽ
ደግሞም ባለ ብልሐት ሁሉን የሠራሽ ።
እማዬ ብናገር ትቈጪለሽ ወይ
የልቤን ራሮት ያንጐሌን ሥቃይ ፤

ኢትዮጵያ    ብዙ ይጫወታል እናትና ልጅ
አደምጥሀለሁኝ ተናገረው እንጂ

ልብ    ይህች መልካም ቈንጆ የጅማ ከተማ
ዘመናዊ ጽዳት ጥበብ ተሸልማ
ልቤን ወሰደችው ድምፅዋ ሳይሰማ
ጠቀሰችውና በጅዋ አቅማመጥ
ሕሊናዬ ሄዶ አልቻለም ሊያመልጥ ።
ሁለት ሦስት ቀን አብሬአት አድሬ
ወግታ ሠቀየችኝ በትዝታ ጨሬ
በባቡሩ መንገድ አረማመዷን
ሳስበው ማረከኝ ወሰደው ቀልቤን
አሳምራ ለብሳ ቀሚሷን ንጽሕና
ከመንግሥት መሥሪያ ቤት በታላቅ ትሕትና ።
አገኘኋትና ሰጥቻት ሰላምታ
ጉዜዬን ሳዘግም ሁኜ በጸጥታ ።
ዐየኋት ከመንገድ ስትሽሞነሞን
ነጭ ሐሯን ለብሳ ስትጠብቅ ሰውን ።
ምንድር ጉድ ነው ብዬ እንዳልሁኝ እልፍ
ልብስ ስትገዛ ዐየኋት ከሱቁ በራፍ
ገበያም ብመለስ መንገዴን ሰብሬ
ስትሸጥ አገኘኋት ልዩ ልዩ ፍሬ ።
መንገደኛም ብትሆን ምንም ብትዛክር

ይህ ዲካህ ማይበል አደረብኝ ፍቅር
፳ በሄድሁበት ሁሉ ከፊቴ እየመጣች
በመንገድ በገቢያ ውል ውል ትለኛለች ።
በሥራ በጽዳት እኔ ብወዳት
ጉዳይ አትለኝም ብዙ ሰው አላት ።
ሀብታም ባትወድ ኑሮ ባይዘኝ ችግር
አብሬአት ለመኖር ደስ ባለኝ ነበር ።

ኢ.ትዮጵያ  እኔ ፍሬ ብዬ ብትጠይቅ ፈቃድ
ጣሊያን የሠራውን አዲስ ልብስ መንገድ
ለብሳ ብቅ ስትል አይገኝም ወንድ
ጅማን የማይጠቅስ ጅማን የማይወድ ።
ከሙሉ በክፍሉ በእጁ ያለውን
አስረድቸሃለሁ እንግዲህ ይብቃን

ልብ  እማዬ ገረመኝ ጥበብሽን አይቼ
በይ እንግዲህ ልሂድ መወድስ ሰጥቼ

## መ ወ ድ ስ ።

የከፋ ግዛት እናት ሁሉን የምትችል
ስታጫውታቸው በደንብ የቄላን ልጆች አትክልት
ጣፋጩ ፍሬ ለሙዝ ታላላቅ ቀጠል ለእንሰት
ለሳቂ ልጅ ጽጌ ረዳ
ደረሰው እንደ ዕድሉ ሁላ አበባ በሀብት
ለደበልም አናናስ
አስመጣችና ጋተች የማርን ወለላ ከቤት
አራዊትሂ ወእንስሳት ሳይሰማቸው ፍርሃት
ታክበው ይፈነጫሉ በከፋ ምድረ ገነት
ገነት ምድረ ከፋ የሚጠብቋት መላእክት ።

## ምዕራፍ ፲ ሐረርጌ ደረት ።

### መግለጫ ።

በቆዳ ስፋት ሦስት የሚያክለው ሰፊው ጠቅላይ ግዛት ሐረርጌ ነው። ደረት የተባለው ስለ ዚህ ነው ፣ ከጨርጨርና ከባሌ በቀር ረጃጅም ዕንጨት አይገኝበትም ። ብዙ በረሃ አለው ። የበረሃው ነዋሪ ብዙ የቀንድ ከብትና ገመል አለው ፤ ወይና ደጋው ቡን ጫት ፍራፍሬ ያበቅላል ። ማነኛቸውም የጠቅላይ ግዛቱ ሀብት የሚገኘው በሰው ትጋት እንጂ በመ ሬቱ ስባት አይደለም ። በዘመናዊ ሥልጣኔ በጣም ገሥግሷል የበረሃ አራዊት ሞልቷል ።

የጉርሱም አውራጃ ደንጋያማ ሲሆን ከጅጅጋ በታች ያለው ወለል ያለ ሜዳ ነው። ስመ ጥሩው ወንዝ ዋቢ ሸበሌ ነው ። መዋትም አልፎ አልፎ አለው ።

አውራጃዎች ፤ ሀ) ሐረር ፣ ለ) ድሬድዋ ፣ ሐ) አዳልና ኢሳ ፣ መ) ወበራ ፣ ሠ) ጨር ጨር ፣ ረ) ጋራ ሙለታ ፣ ሰ) ጉርሱም ፣ ቀ) ጅጅጋ ፣ በ) ባሌ ናቸው ። ዋና ከተማው ሐረር ነው ።

ወሰን በሰሜን ከወሎና ከሸዋ ፣ በምዕራብ ከአሩሲና ከሲዳሞ በደቡብና በምሥራቅ ከሱማሌ ጋራ ይዋሰናል ።

ዓለም ነሆለለ ተማረከልሽ
ጡትሽን ደሳሰ ቱርክ አደነቀሽ
ተገልጦ ቢታየው ሳንቃው ደረትሽ ።
ደረት ጡትሽን ዐይቶ ባላለቀ ሰው
መጋረጃ ሚሆን ልብስ ብታለብሺው ።
ሽማግሌ አበደ ጀግና ተሠቀየ
ሐረርጌ ደረትሽ ተገልጦ ስላየ
ፍራፍሬ ጡትሽን ዐይን እንዳይበላው
አልብሺው እናቴ ማንም አይየው ።
ደረትሽ ተገልጦ ያየው ሁሉ ዓለም
ምነው ባገኘሁት የማይል የለም ።
እመ ለቀንጅናሽ ሰዎች ሲጫወቱ
ዓለሙን ማረከው ደረትሽ ስፋቱ ።
ደረትሽን ገልጠሽ ብታሳዪው ድሮ
ቱርክ እንኳ ጐረምሳው አነሣ አምባጓሮ
ደረትሽን እያየ ሲያስብ ሌላ ሌላ
ልጅሽ ደረሰና ቢያቀምሰው በዱላ ።
አንችም ባትወጂው ወግና ጨልንቆ
አገር ጥሎ ሄደ ውበትሽን ለቆ ።
እሱም ጥሎሽ ቢሄድ ጣሊያን ጐረምሳው
ሱማሌ ላይ ሁኖ ሊያጭሽ አማረው

ይህ ሁሉ ፍዳ ይህ ሁሉ ሥቃይ
መጣ በደረትሽ ተገልጦ ቢታይ ።
ያለፈውን መሳይ እንዳይደርስብሽ
ጋቢ ቅጠል ገዝተሽ ደረትሽን አልብሽ ።
ምንም ውብት ቢሆን ለሰው ልጅ ደረቱ
እንዲታይ አልወድም ተገልጦ ስፋቱ ።
ቁመቱ ስፋቱ ዲካ የሌለው
የደረትሽ ስፋት ዓለምን ደነቀው ።
በሰፋት በቁመት ባየው ብተቸው
ካካልሽ አንድ የለም ደረትሽን ሚያክለው ።
የደረትሽ ስፋት ቢከፈል በስልት
ያክልልሽ ነበረ ሦስት አካላት ።
ስለዚህ እማዬ ስሚኝ እባክሽ
ራቁትሽን ያየ ደረትሽን ገልጠሽ
አልፎ ሃጁ ሁሉ እንዳያውክሽ
አልብሺው ሸፍኚው ታላቅ ልብስ ገዝተሽ ።

ኢትዮጵያ　ደረቴን ሸፍኚ አንተ እንደምትለው
የፈለገ ላይቀር ማፈሬ ለምነው።
ባሌ ንጉሥ ባለም ጀግናው ስመ ጥሩ
ችግር የማይፈታው ልጄ ወታደሩ
መራሩ ሳለልኝ በረሃ ደፋሩ ።
በጥይት ሚቄላ በመላ ሚፈታ
ማይሰጥ ለጠላቱ ዕረፍት ላንዳች አፍታ ።
እንደዚህ ከሆነ የልጄ ጠባይ
ባዳውም አይደፍረኝ ደረቴ ቢታይ ።
ምንም ብወለወል በጌጥ ብሰናዳ
እኔም ካልጠቀስሁት አይደፍረኝም ባዳ ።
ደረቴን ገልጬ ምንም ሳላለብስ
በዓለሙ ገበያ ብውል ስፋሰስ ።
ሌላው አይደፍረኝም ልጄ አትቸገር
በሕግ ካገባሁት ከባሌ በቀር።
ዓለሙ ሲያደንቀው እያየህ መልኬን
እንዴት ልሸፍነው ሐረር ደረቴን ።
ደረቴ ሐረርጌ ላለም ቢታየው
ፍራፍሬው ጡቴ አንሰፈሰፈው ።

ዓለሙ በሞላ ያልተወለደው
የጡት ልጅ ነኝ አለ ጡቴን ሊጠባው ።
ቀሚሴን ገዝቼ ብሸፍነውም
ከእግር እስከ ራሴ ለብሼ ስቆም
ሰፋቱን በግምት ያውቀዋል ዓለም
ስለዚህ ብሸፍን ዋጋ የለውም ።

ልብ ደረትሽ የታየ ተገልጦ ለሰው
ላይ ላዩ ነው እንጂ ታቹስ ሽፍን ነው ።
የጡትሽ በታቹ ባሌና ጨርጨር
ተደቡኖልሻል በቀሚስሽ ዱር ።
ከጡት በላይ እንጂ ከጡት በታችማ
ለብሰሽ ብትታይው የባሌሽን ውድማ ፡
ዓለም ተደነቀ ፍጥረት ተገረመ።
በጨርጨሩ ልብስሽ ሕዝቡ ተደደመ።
የደረትሽን ስፋት ባጭር ካወጋን
እመ እስቲ ንገሪኝ የታቀፍሽውን ።

ኢትዮጵያ እንግዲያስ አዳምጠኝ ሁሉን እንድትሰማ
ብዙ ወይነት ፍሬ ነው የታቀፍሁትማ።
ካታክልቴ ሁሉ እኔን ሚያስጠራኝ
ባለም የታወቀ ጥሩ ቡና አለኝ።
አፍልቶ ሲጠጡት የሐረርን ቡና
ይፈታል አንደበት ያነቃል ልቡና ።
በደንብ እያፈላ የለመደው ሰው
ከሐረርጌው በቀር ሌላው አይጥመው ።
አርሜ ኰትኵቼ መከራ ሳልሠጋ
የደከምሁበትን ክረምትና በጋ
ሁሉን ያስረሣኛል የቡናዬ ዋጋ ።
ዘምኜ እኖራለሁ እንደልቡናዬ
መቼም አልቸገር ሳለልኝ ቡናዬ ።
እህልም ቢታጣ ቡናውም ቢጠና
ሽምቼ እበላለሁ ቡኔን አቀናና ።
ቡናዬ ታወቀ በዓለም ተወደደ
በባቡር በመርከብ በአእሮጵላን ሄደ ።
ሳይላክ አይቀርም እንደ ቴሌግራም
በነፋስ መሣሪያ ዓለም እስከ ዓለም ።

ሐረርጌን አነሣ ፍጥረቱ በሞላ
ቡናዬን አፍልቶ የቀመሰው ሁላ ።
በጣም ይጣፍጣል ለቀመሰው ሰው
የቡናዬ ቅጠል ቍጢና ሆኗው ።
ዝነኛው ቡናዬን አንተም ብትቀምሰው ።
ልትለየው ይቻላል ጣዕሙን ከሌላው
አሁንም ቍጭ በል አፍልቼ ልስጥህ
ግምት እንድትሰጠው አንተው ራስህ ።

ልብ
እማዬ አትድከሚ አፈላ ብለሽ
ሰጣኛለችና በቀደም ልጅሽ ።
እውነትም እናቴ በጣም ይጣፍጣል
ድገሙኝ ድገሙኝ አትለዩኝ ይላል ።
መዓዛውና ጣዕሙ ለቀመሰው ሰው
ከሌሎቹ ሁሉ በጣም ልዩ ነው ።
ሽታና ላህዩ እንዲህ ያማረው ፥
የተሠራበቱ ጥንቃቄው ምነው ።

ኢትዮጵያ
በሥራማ በኩል ባለሙያ ነኝ
ሣርም ስኰተኵት ማነው የሚያኽለኝ ።
አርሜ ኰተኵቼ በጋና ክረምት
ፍሬውም ሲደርስ በመከር ወራት
ብስልና ጥሬውን በእጄ እየለየሁ
ሌት ተቀን ተግቼ እለቀመዋለሁ ።
ካደረቅሁ በኋላም በጥንቃቄ አስጥቼ
አስቀምጠዋለሁ ጐተራ ከትቼ ።
በደንብ ተጠንቅቄ ካስቀመጥሁትኝ
ወቅቱን አስተውዬ ጊዜ ሲመቸኝ
በግመሌ ጭኜው ገበያ ብወርድ
ያላንዳች ክርክር ይሸጣል በውድ ።
ከቡናዬም ሌላ ውዱ ጫት አለኝ
ባረብ ሀገር ሁሉ የሚያስከብረኝ ።
ቈፍሬ ባካፋ ኰትኵቼ በዶማ ከተከልሁት ጫት
ከመልማት በቀረ አያውቅም መጥፋት ።
በጣም ይጣፍጣል ጣዕሙ ግሩም ነው
ቀንበጡን ቀራርመህ እስቲ ቅመሰው ።

ልብ
እማዬ ቀመስሁት ይለዘልዛል

ደግሞም እንደ አምባጮ ይከነክናል ።
ሽጪው እንጂ ላረብ ወረቅ እንዲሆንሽ
ለክስካሳ ምግብስ አልወድም ልጅሽ ።

ኢትዮጵያ እኔ ምን ቸገረኝ ብትወደው ብትወደው
መሐመድ ሳለለት ሌት ተቀን ሚቀመው ።
ለምልሞ ከታየው ከግር እስከ ራሱ
ዐረብ ይወደዋል እስኪወጣ ነፍሱ ።
በግመል በባቡር በመርከብ ባየር
ይጫናል ለየመን በታላቅ ክብር ።
በቡናና በጫት የማመጣው ወርቅ
ታላቅ ሀብት ነውና ጫትን አትናቅ ።

ልብ ወርቅ የሚሆንሽን ትልቁን ንብረት
ለዘለዘ አልሁ እንጂ እኔ መቸ ናቅሁት ።

ኢትዮጵያ አንተን ባይጣፍጥህ ስላልመደኸው
ባየኸው አሕመድን ተግቶ ሲቀመው ።

ልብ መቃምስ ይቃመው እንደ ባሕሪው
ቀንበጡን አላምጦ ምነው ሚሰማው

ኢትዮጵያ ይቅም ይቅምና ጠግቦ ሲመረቃ
ሥራ ለመጀመር ጉልበቱ ሲበቃ
በትጋት ተነሥቶ ሲያዋረገርገው
እንዴት ያለ ሥራ ነው ኀይሉን ሚያግደው ።
አንጐሉ ከነቃ የጫት ቅጠል በልቶ
ሲጣደፍ ከዋለ ቀኑን ሙሉ ተግቶ
ቤቱን ይመለሳል እጅግ ሥራ ሠርቶ ።

ልብ አንችም በውድ ሽጭው እሱም ይቃመው
የጫቱ ወሬአችን እስከዚህ ይብቃው ።
ስለሌላው ፍሬ ስለታቀፍሽው
በዩ እስቲ ንገሪኝ ሁሉን ልወቀው ።

ኢትዮጵያ ፍሬውን ሰብስቤ ታቅፌዋለሁ
ልታይም ከፈለግህ አሳይሃለሁ ።
ሙዝና ብርቱካን ደግሞም በኸረ ሎሚ
አለ በጐንፌ ለሰው ልጅ ተሰማሚ ።
ቈማጤ ጣፋጩ ሲያዩት አስቀያሚ
ለቀመሰው ሁሉ በጣም አስገራሚ ።
በኤረር በጐታ በሐረር ሁሉል

አምሳያ የለውም የምተክለው ተክል ።
ተጋኜ አንጀርን አፍርቶ ስታይ
ከዚህ ሚወዳደር አንጐል የሚይሰይ
ያለም ባልመሰለህ ባለም ላይ ሲሳይ ።
ፍሬዬን ሰብስቤ በጋራ ሙለታ
አስቀምጠዋለሁ በኤረር በጐታ ።
በባቢሌ ዐውደማ በሁሉል እርሻዬ
አትክልቴ ይጋፋል እንደ ልቡናዬ ።
ደግሞም ድሬዳዋ ልውረድ ለገሐሬ
ዘርግሬ እንዳሳይህ ልዩ ልዩ ፍሬ ።
ብርቱካን መንደሪን ትርንጎ ሮማን
በጣም ያስደስታል ብታየው ሁሉን ።
በጨርጨር አውራጃም ባለሙሉ ዝና
ሚገኘው አትክልቴ ይደንቃል ልቡና ።
ትጉሁ ገበሬ ተከለ ሐዋርያት
ጠንክሮ ያለማል ልዩ ልዩ አትክልት ።
እንዲህ ላለው ልጂ ይገባል ምስጋና
ገበሬን ለመምራት ይማስናልና ።

፲

**ልብ**

እመ አትቀየሚኝ ስለተጋንሽ
ያየሁትን ባጭሩ እኔም ልነግርሽ ።
የማላውቀው መስሎሽ እስቲ አትገረሚ
አይጐዳሽምና ስሜቴን ብትሰሚ ።
ትላትና ማታ ሂጂ ለባሕሬ
ስውጥ አመሸሁኝ ልዩ ልዩ ፍሬ ።
ፍሬው ስለጣመኝ ያትክልቱን ዕንጨት
ልልጠው ነበረ እንደ ቋያ እሳት ።
በእጂ እያገበሰበስሁ ዐይኔ ያየውን
ስወለውለው ዋልሁ ተክሉን ሙሉ ቀን ።
ከዚህም ወጥቼ በኤረር በጐታ ፥
በሐረር ባቢሌ በጋራ ሙለታ
በበላሁት ፍሬ ተሰማኝ ደስታ ።
ባዝመራሽ መካከል ተክልሽን ባገኝ
ገነት በቁመና ገባሁ መሰለኝ ።
ተከለ ሐዋርያትም አንች እንዳልሽው ሁላ
ብዙ ተክል አብቅሏል ጥሬው የሚበላ ።

ሁሉንም ብታውቂው የሚሠራውን
አድምጪ ልንገርሽ እመ ስሜቴን ።
፱ እንዲህ ያለ ትጉህ በሚሠራው ሥራ
እንዴት ያስደስታል ገበሬ ቢመራ ።
ትጉሁ ገበሬ ወልደ ሐዋርያት
ወስኖ ሰጥቶታል ለሁሉም ሰዓት ።
ሙያውን ልጐበኝ ሂጄ እኔም ድንገት
ያትክልቱን ልምላሜ የሰብሉን ውበት
አድንቄ መጣሁኝ የርሻውን ስፋት ።

<u>ኢትዮጵያ</u> እንዲህ ምታደንቀው በጽሑፍ ደባይ
ተክለ ሐዋርያትን ታውቀዋለህ ወይ ፧

<u>ልብ</u> ሲወራ ሰምቼ ያዝመራውን ዝና
ጐብኝቼ ለመምጣት ሄድሁና ታች አምና ።
እየተመላለስሁ ገብቼ ባየው
እንኳንስ የሚበልጥ አምሳያም የለው ።
ሙያው ቢማርከኝ ሥራው ቢገርመኝ
ልጠይቀው ብዬ ወደ ቤት ሄድሁኝ ።
ወዲያውም ደርሼ ብጠይቅ አሽከር
አይገኝም አለኝ የለም በሀገር ።
ይህን እንደሰማሁ እኔም እያዘንሁ
የምዞርበትን ጕዞዬን ቀጠልሁ ።

<u>ኢትዮጵያ</u> በሥራው በግብሩ እንደ ገመትኸው
አዛዥ ብትሆን ኑሮ ምን ባደረግኸው
ሀብታም ብትሆን ኑሮ ምን በሰጠኸው ፧

<u>፲) ልብ</u> አዛዥማ ብሆን እንዲህ ላለው ሥራ
በጥበብ በውቀቱ ሕዝቡን እንዲመራ ።
ሱማሌ ሲይዘው ሚያወለውለው ፤
ራሱም ሲያረባው እንዲያ ያማረው
ባለም ማያ ኮሌጅ ያጠቃው <u>አጋገን</u>
በሬውና በጉ ሁሉም እንዲጠገን
ነጭ እንዳያጠፋው እየቀጃበረ
የእርሻችን ኃላፊ አረገው ነበረ ።
ደግሞም ከዚህ በላይ ሀብታም ብሆንማ ፤
ግብርና እንዲስፋፋ ሀገር እንዲለማ ።
ገንዘብ እሰጥና እንዳይቸገር

የልማት ኋላፊ አረገው ነበር ።
በዘመናችንም በጣም የተማሩ
ቊጠባና ዕድገትን የተመራመሩ
ባፍ ያወራሉ እንጂ እንደሱም አልሠሩ ።
በዕውቀቱ በግብሩ በቤቱ ሥርዓት
ሳላውቀው ናፈቀኝ ተክለ ሐዋርያት ።
ራሱን ከቻለ እግዜር ከሰጠው
ወገኑን ሰብስቦ እንደተቻለው
ሠርቶ ሲያሠራ ነው ሰው ሚመረቀው ።
ባዝመራው መካከል ልዩ ልዩ አትክልት
ቊጥሩ ማይታወቅ በጣም ብዙ ዐይነት
ተክሎ አልምቶ ሳለ ጫት የሌለበት
፲፩ እማዬ አልገባኝም የዚህ ምክንያት ።
ከቶ ለምን ይሆን ጫት አለመትከሉ ፤
ወርቅ አይሆነውም ወይ እንደሌላው ሁሉ ።

**ኢትዮጵያ** የዚህ ምክንያቱ በጣም አጭር ነው ።
ጫት ድኅነት እንጂ ረብም የለው
ብዙ ሚያፈራውን አትክልት ብተክለው
እጅግ ሚያመርተውን እህል ብዘራው ።
ዳኅናውን መሬቴን የማርሰውን
ለጫት ቅጠል ብዬ ለምን ይቦዝን ፤
እያለ ካዝመራው ታጥቆ ተነሣና
ነቃቅሎ ጨረሰው አደረገው መና ።
ምንም ባውቀው ቅሉ የተሰማህን
እንዳወራህ ሌላ እስከዚህ ይብቃን ።

**ልብ** አዳዲሱን አውሪኝ እስቲ በይ እማዬ
ወሬሽን ለመስማት ጓጓ ልቡናዬ ።

**ኢትዮጵያ** በጨርጨር በባሌ በሰፊው አውራጃ
አለኝ ብዙ አዝመራ አንጐል የሚያጃጃ ።
ሕሊና የሚሰይ የሚሰልብ ልቡና
ባለም የታወቀው በጌ ባለዝና ።
ባየኸው በባሌ ፀሐይ ሲመታው
ሞራው እያነቀው መሄድ ሲጨንቀው ።

**ልብ** ዐየሁት ገረመኝ በግሽን በባሌ
የከብት መንጋሽንም በዋቢ ሺበሌ ።

በዋቢ ሸበሌ ዳር ለዳር ሳለሁ
ይመስለኝ ነበረ ገነት የገባሁ።
፲፱ ጨውን ከዚያው ዝቆ ያምበውንም ሐራ
ይመስላል ነጭ ጥጥ የፍየሉ ሞራ ።
በሬውም እንዲሁ አምበውን ከበላ
ስቡ ካላነቀው አይመኝም ሌላ ።
እህል ወይስ አትክልት ምኑን ልናገር
እንዲያው ዕፁብ ድንቅ ነው የባሌሽ ነገር ።
የእንስሳትን ወገን ካነሣነ ዘንዳ ፣
ምንም አዲስ ባይሆን ባንች ዘንድ እንግዳ
እመ ያየሁትን ትንሽ ልዘላብዳ ።
እንዲያ ሲያወለውል ላሙና በሬው
በጣሙን ገረመኝ ዑጋዴን ባየው ።
መንጋው ሲያሽመለምል ተዦሮ ሲያዩት
አከላቱ ሁሉ ይመስላል ወሊት ።
እንኳንስ አጋገን እከክ ሊያጠቃው
በለሙሉ ጤና ታላቅ ጉሽ ነው ።
በጉ እንዴት ያምር ለተመልካች ሰው።
አካሉ ነጭ ሳለ ሚያወለውለው
ዓለም ማያ መጥቶ አጋገን ፈጀው ።
በዘላንነቱ ስሙ የተነሣ
ብዙ ከብት ያረባል አዳልና ኢሳ ።
የበረኻ መርከብ ቊጥር የለሽ ግመል
ባዳል በሱማሌ ሲተም ይታያል ።
፲፫ በወበራ ሜዳ በሐረር በረት ፣
ባዳልና ኢሳ በሱማሌ ቤት ።
በጋራ ሙለታ በጉርስም በባሌ
በሰፊው ውጋዴን ደግሞም በሱማሌ ።
ታሥሮ ሚቀለበው ሊሸጥ ለፍሪዳ
ደጋግሞ ይሸኛል የሆድን እንግዳ ።

ኢትዮጵያ ሌት ተቀን ኰትኵቼ መሬቴን በሞላ
እዘራዋለሁኝ ያማረ ማሽላ ።
ያትክልት ያዝመራ ወግ እስከ ዚህ በቀቶን
ሴማዩን ለውጨ ላውጋህ ሌላውን ።

ልብ ሁልን ተናገሪ እሰማሻለሁ

ከወንበር ቀጭ ብዬ ቡና እየጠጣሁ ።

<u>ኢትዮጵያ</u> ከሰማህ ቀጭ ብለህ አንት ካልደከመህ
ወግማ ምን ገዶ ሳለሁ እናትህ ።
በውጋዴን ቈላ በኢሳ ባዳል
የበረሃው አውሬ ይጥመለመላል ።
አንበሳና ነብር አነር ማሻንብል
እንኳንስ <u>ቱሲውን</u> ጀግና ያስፈራል ።
ሚዳቋና ሰሳ የሜዳ ፍየል ፤
ከቡኸር <u>ከትኙ</u> አብሮ ይበላል ።
አጋዘን ቀጭኔ ታላላቅ ድኩላ
ሚዳውን ያለብሳል እንደዚሁም ሳላ ።
፲፬ የዕፀዋት ልምላሜ ዛፍና ዕንጨትም ፤
በባሌ በጨርጨር የሌለ የለም ።

<u>ልብ</u> ስለዛፍ ስለተክል ደግሞም ስላዝመራ ፤
መቼም አያልቅና ቢተረት ቢወራ ፤
አባክሽ ንገሪኝ ከጥበብሽ ሥራ ።

<u>ኢትዮጵያ</u> ትምህርትና መንገድ ዘመናዩን ካልህ
ደረቴን ሚመስል የት ታገኛለህ ።
በጥበብ ጕዳና መንገዴ እንዲቃና
ጠቅል ይረዳኛል ያለዕረፍት በጠና ።
ስለዚህ ሚያኰራ የሚያስደስተኝ
ዕውቀት ሚዛቅበት ትምህርት ቤት አለኝ ።
መንግሥት ፤ ቤተ ክህነት ፤ እስላም ሚስዮን
ተባብሮ ይሠራል በትምህርት ወገን ።
በሐረር ከተማ ስንፍና ድካም
ምሎ ጥሎ ሄደ በመድኀኔ ዓለም ።
ከሲኦል ስንፍና የዳነው አዳም
በመድኀኔ ዓለም ነው ከዚህ ቀደምም ።
ድንቍርና ሌባ በኀይለ ሥላሴ
ተፈጥሞ ጠፋ ደስ ይበልሽ ነፍሴ ።
ድንቍርና ነግሦ በቀድሞው ዘመን
ካገር እንዳይገኝ ያደረገውን
ያገራችን ዕውቀት መንፈዊውን
መልሶ ተክለው ራስ መኰንን ።
፲፭ በትምህርት ብትገርፈው ያች የሽ እመቤት

አይደግመኝም አለ የሴቶች ሀኬት ።
ማሠልጠኛ ገብተው ተግተው መምህራን
ሲያጦኑ ደስ ይላል መላ አከላትን
በወታደር ኮሌጅ እጩ መኳንንት
ሀገር ሊጠብቁ ሊረዱ መንግሥት
ዘዴ ይማራሉ ያላንዳች ዕረፍት ።
ሕንፃው ብቻ በቃኝ ሰውን ሚያስጐመጅ ፡
ዓለማያ አለልህ የእርሻዬ ኮሌጅ ።
ሥራው በጣም ዕፁብ የአዲሱ ዘመን
አእምሮ ይሰያል ያጓጓል ልብን ።
ግሩም ነው ይገርማል የግቢው ነገር
ደግሞም ከዚህ በላይ ደጉ አስተዳደር ።
ተላላኪ እንዳይሮጥ በየክፍሉ መጥሪያ
አለለት ተስፋፍቶ የራድዮ ማጉያ
ማማሩን ውበቱን መግለጡ ቸገረኝ
ጌጥ የማጐላበት ቃላት እያጠረኝ ።
ብዙ ዓይነት መሣሪያ ቍጥር የሌለው
በትጋት ሰብስቧል በታ እስቲጠበው ።
እንኳን ሥራ ውሎ ሲያርሱ በግብርና
እንዲያው ብሉ ይላል የበዩ ንጽሕና ።
አበባ ተጋኑ ዕውቀት ያበጀው
በጣም ያስደስታል ለለመደው ሰው ።
ዶሮ ከናውራዋ ቤት አሠራችና
ከቄጢ ወረደች ያላንዳች ምስጋና ።
በሬ በጅጅጋ እሣሩ ሲያጥረው
ባለም ማያ ኮሌጅ ገንፎ ተረፈው ።
ወረዳው ሁሉ አለው አንደኛ ደረጃ
ብዙ ትምህርት ቤት እንኳንስ አውራጃ ።
የግል ተማሪ ቤት ዓለም ያወቀው
የሚስዮን አለ በየከተማው ።
በሐረር በደደር በጋራ ሙለታ
ደግሞም ድሬድዋ በደንበኛው በታ
መነናዊትና ካቶሊክ ስዊድን
ጠንክሮ ይታያል የሰውን ነፍስ ሲያድን ።
ክርስቶስ ሲያስተምር ይታያል ሕዝቡን

ዕረፍትን ሳይሻ ተግቶ ሌት ተቀን ።
ትምህርት ቤትና ጥሩ ሐኪም ቤት
መሥርቶ ይሠራል ያ መነናዊት ።
ከምግባሩ ጋራ መድኃኒት ቢያገኝ
፲፪ ልጅም ተፈወሰ እኔም ደስ አለኝ ።

ልብ　በብዙው አወጋን ስለትምህርትሽ
የነገርሽኝ ይብቃ እማዬ እባክሽ
ተርትረሽ ንገሪኝ መንገድ እንዳለሽ ።

ኢትዮጵያ　መንገድስ ከጠየቅህ በያወራጃው አለኝ
ለመንሸራሸሪያ ምንም አያስቸግረኝ
አቀበት ቍልቍለት ሸንተረር በሞላ
መኪና ያስኼዳል እንደ ሜዳ ሁላ ።
የመንገዴ ጥዳት በጣም ያስገርማል
አዲስ መናፈሻ ከተማ ይመስላል ።
ከሸዋ ጅቡቲ እስከ ደምበርበት
አለኝ ባቡር ሐዲድ የምኰራበት ።
ከሐረር ጅጅጋ ደግሞም ቀብዲሐር
የምፋሰስበት እንደምን ያምር !
ጕርስም ድሬዳዋ ወበራ ደደር ፥
ሲሻኝ እበራለሁ ያላንዳች ችግር ።
ከባቡሩ ወርዶ ሚሶ ዐስበ ተፈሪ
ሚወስድ መንገድ አለኝ የሰውን ልጅ አኵሪ ።
ከሐረር ተሳፍሮ በጋራ ሙለታ
ነፋስ ሲቀበሉ ይሰማል ደስታ ።

ልብ　ሽርሽሩን ዐየሁ ወግሽን ሰማሁ
አንዳች በጐደና ማንም አላየሁ ።
የመፋሰሱ ወግ እመ ይብቃኝና
እስኪ ትንሽ አውሪኝ ከያዝሽው ባልትና ።

ኢትዮጵያ　ለባልትናውማ መቼ ተቸግሬ
ሳሉልኝ ልጆቼ ሱማሌና አደሬ ።
ምንም ዘላን ቢሆን የሱማሌ ኑሮ
ሚስቱ ሳለችለት መቼ ተቸግሮ ።
መንጋው የሚባለው ካገኘ ሣር ውኃ
ያላሳብ ይኼዳል ካፈተተው ሻኃ ።
ላምነትና ጀንዲ ስጋጃ ወላንሳ

አስመስላ ሠርታ የይገኛ ገሳ
ሚስቱ ትጭንና በጠያር ገመል
ይዛ ትደርሳለች ምንም ሳይጐድል ።
ደገኛው ጅንያ የእህል መጫኛው
እንኳንስ ማሽላ ጤፍ ማያፈሰው
ልባማ ሱማሌ የሰራችው ነው ።
ለያያታ ለያያታ ሠርታ ክንፍ ክንፍን
ጭናው ትሄዳለች ሱማሌ ቤቷን ።
ያበጀችው ምንጣፍ የሣሩ ዳውጃ
በውበት ይልቃል ከሕንዶች ስጋጃ ።
አቆማዳም አላት ደግሞም ወተት ዕቃ
የወገኗ ኵራት የበቃ የነቃ ።
ሱማሌዋ ልጇ እጅግ ልባሚቱ
ታሰናዳዋለች ሁሉን በያይነቱ ።

**ልብ** እውነትም እናቴ እንደሷው ትጋት
ምን ትሠራ ነበር ባሏ ቢረዳት ።
ቤት ሠሪዪቱ እሷ ናት ምግብ አሰናጂ
ወንዱስ አፋዳሽ ነው ክብት መጠበቅ እንጂ ።
ሱማሌን ያላየች በሌላው አገር
ሴት ጡረተኛ ናት የባለዋ ችግር ።
ካገሬ ሰምቼ የሙያዋን ዝና
ዐይቼ ልረዳ እኔም መጣሁና
አቅርብላት ጀመር በሰፊው ምስጋና ።
እያልሁ ታታሪ ነሽ ልባም በውነት
አሁን የት ይገኛል እንዳች ያለ ሴት ።
ሥራዋ ይገርማል ይደንቃልም እኮ
ቤት ጠቅልላ ስትሄድ እንዳጭር ብልኮ ።
ዕቃዋን ባንድ ግመል ቤቷን በጠያር
ጠፍራ ስትጓዝ እንደምን ታምር ።
ትመስላለች መቼም የተማረ ጦር
ቤት ድንኳኗን ተክላ በቅጽበት ሰትሰፍር ።
ገረመኝ ደንቀኝ ባይ ይኸን ብልሃት
እናቴ ንገሪኝ ማን አስተማራት ።

**ኢትዮጵያ** እሷው ተፍጨርጭራ አወጣችው እንጅ
ይኸን ሚያስተምራት የላትም ወዳጅ ።

ወደ ሐረር ውጣ አደሬ እኅቷን
ዐይተህ እንድታደንቅ የቤት ሥራዋን ።
ሞሰብ ቀለምሻሹ ላዳን ወራንታው
ዕንቅቡ ሌማቱ ዐይን የሚያጃጃው
ሕሊና ያጠፋል ይማርካል ሰው ።
ለጠብና ወንፊት ሰፌድና ቁና
ሙዳይና አገልግል ሥራው የተቃና
ሰፋችው ባለላ ለታሪክ ለዝና ።
ሁሉንም ሰምላ በእየግድዳው
ዕቃዋን ባንድነት ሰቅላ ባየኸው ።
ዐይን ያነሆልላል ልብ የቢዝዛል
ይኸ ሁሉ ስፌት ከቤት ሲሰቀል ።

ል ብ  አቤት አቤት ዕፁብ እመ ገረመኝ
ሙያዋን ዐይቼ በጣም ደነቀኝ
ጥበቧን አጥንቼ በጣም ደስ አለኝ
እንደሷ የሰፋች የትም አትገኝ ።
ከሁሉም ሚደመኝ ከሙያዋ ሌላ
መልኳ ዋጡኝ ሲል ነው እንደ ሎምበ ሾላ ።
ያማረ ብርቱካን መሳይ ሰውነቷ
ምንም አታውቅ ይላል ሥራ በሕይወቷ ።
አንድ ሰዓትም ሳታርፍ ሌት ተቀን ስትሠራ
ትወደደራለች ከንጋቷ ጮራ ።
አንጐሌ ተሰየ ዐይኗን ብትከፍተው
ናላዩ ዞረብኝ ጥርሷን ብትገልጠው ።
አእምሮዬ ጠፋ ባይ እግር ባቷን
አካሄዷንና አረማመዷን ።
ክናዷ ሙርሙኝ ነው ተረከዟ ክት
እንዴት ያል ልብ ነው ይህን ሚመክት ።

ኢትዮጵያ  በጥበብም በኩል አቡጀዲድና ስሚቶ ፋፍሪካ
አለኝ ድሬዳዋ ልብን የሚያረካ ።
ተራራውን ፈልጦ ሸርክቶ አንድነት
አልሞ ሰልቆ አድርጎ ዶቄት
አቡክቶና አላቍጦ በውኃው እንፋሎት
ቀቅሎ አንገርቦ አብስሎ በእሳት
ያወጣል ስሚንቶ ልዩ ልዩ ዐይነት ።

ደንጊያውን ሚፈልጠው ሚፈጨው ሚቄላው
ማንም ሰው አይደለ ሐዲስ መኪና ነው ።
ሲያወጣና ሲያወርድ የድንጋይ ኩረት
ይመስላል ትሬንታ የተጫነበት ።
የሚያምም በረዶ የሚዝገመገም
ሊያጠፋ የመጣ ይህነን ዓለም ፤
ደግሞም ሲንከባለል እንደናድ በረዶ
ውኃን የሚቀዳ የበረሃ ዘንዶ
ያስንቃል በግርማው ላየው በስተማዶ ።
በዚህ ሁሉ ድካም ጋግሮ ያበስልና
ፈጭቶ ያደርገዋል ዶቄት እንደገና ።
ጠራርቦ ጠራርቦ ለጡብ ለማዘን
ፈላጊ ሲመጣ ይሸጣል ሁሉን ።
በወረቀት ከቶ በጥሩ ጆንያ
ያንጫርረው ጀመር በዓለሙ ገበያ ።

**፳፪** አልተሰባህ እንደሁ ይህ የምነግርህ
እየዘርህ ገምተው አንተው ራስህ ።

**ልብ** ተሰባኝ እናቴ ያወራሽኝ ሁላ
ዞሬ ስላየሁት ሥራውን በሞላ ።
የሚያሽከረክረው ሁሉን መዘወር
በጣሙን ይገርማል ይህ መንኰራኵር ።
ዕቃ ቤት ግምጃ ቤት ቢሮውንም ዐየሁ
በሥራው ተደነቅሁ በጣም ተገረምሁ ።
ግሩም ነው ዕፁብ ነው እንዲህ ሲጣደፍ
ሌት ተቀን ይሠራል አንድ ቀን ሳያርፍ ።
ዐይተን ተረድተነው ይኸ ከገባን
ሂደን እንረዳው ያቡጀዴውን ።

**ኢትዮጵያ** በዚያኛው ፋፍሪካስ በጣም የሚያኰራ
አለኝ ብዙ ጥበብ ልዩ ልዩ ሥራ ።
መኪና እየረዳኝ ዳምጨ አሳስቼ
ነድፌ አመልምዬ ፈልቅቄ አበዝቼ
ፈትዬና አቅልሜ ድርና ማጉን
አለብሰዋለሁኝ በመላ ሕዝቡን ።
ፍራሽ አቡጀዲድ ብርድ ልብስ የሌት
ስሠራ ባየኸኝ ያላንዳች ዕረፍት ።

ሀገሩን ሲገዛ ስንፍና ደንቆሮ
ሚሰደበው ልጇ ከዚህ ቀደም ድሮ ።
በውዕቀቱ በግብሩ የሚነቀፈው
ወደ ዚህ ቤት መጥቶ ታየና ሥራው
ደመወዙ በዛ ሰው አከበረው ።
አዲስ ግንብ ተሠራ ሥራ ተከፈተ
በሺህ የሚቈጠር ብዙ ሕዝብ ከተተ ።
ዓለሙ ቦዝኖ እንደዚህ ሲተች
ቀጠረ ፋብሪካው እልፍ ሠራተኞች ።
ሥራው እንዲስፋፋ ግብሬ እንዲቀናኝ
አዳዲስ መኪና አስመጣለሁኝ ።

<u>ልብ</u> እውነትም እናቴ እንዲህ ላል ተግባር
ሊለፉ ይገባት የሰው ልጆች ዘር ።
ሽማ ዕቃው በሞላ ብጥሩ መዳን
ተሠራሁኝ ይላል ባዲሱ ዘመን ።
መወርወሪያው ፈጣን እንደ አንጐል ሐሳብ ።
አእምሮ ሲያስበው ያስደንቃል ልብ ።
አለሽ ባልንጀራው ቀልብን ሚያስጐመጅ
የሐዲዱ ጣቢያ የባቡር ጋራጅ ።
መዘወሩ ቢዞር ፋፍሪካው ሲያጓራ
ይመስላል ከዚሁ ባቡር የሚሠራ ።
መሥሪያው መጠገኛው ማቲ ነው ዕቃው
ስሙንም አላውቀው እንኳን ልቈጥረው ።
መሣሪያውን ሁሉ እየዘርሁ ባየው
ልቤ ተገረመ ዐይኔ ሰለቸው ።

፳፩ የልጆችሽ ሙያ እንደዚህ ቢሆን
አንጐሌን ሲማርክ ሲገርመው ልቤን
እንዴት በደነቀኝ ባይማ ያንችን ።
በልጅ ላይ ይታያል የወላጅ አመል
የጠንቃቃ ጐበዝ ያሳዳጊ ባህል
ትርክርኩም ኑሮ አለል ዘለል ሲል
ትውልድ መነጻር ነው ሁሉን ይገልጣል ።
ላስተዋይ ግልጽ ነው የወላጅ ስንፍና
ያልተቀጣው ልጁ ሲሠራ ብልግና ።
አንች ያሳደግሽው ቅጡና ቅንቱ

ሙያሽን ያስረዳል የሐረርጌ ቄቱ ።
ዓለም ባደነቀው ኀይሉና ትጋቱ ።
ልጅሽን ስላስተማርሽ ያማረ ባልትና
እመ እሰጥሻለሁ መወድስ ምስጋና ።

## መወድስ ።

የብዙ ሕፃናት እናት ብሔረ ሐረር
ልጅን አሳድግ ብለሽ ተጋን በመኰትኰት ስትኖሪ
ይመስላቸው ነበር ሰዎች ታላላቅ ሥራ ማትሠሪ
አሁን ግን ሁኖልሻልና
ጡትሽን ጠብቶ ያደገው ወልድኪ ተፈሪ
በግርማ ዳር እስከ ዳር
ያላንዳች ሐሳብ ዘወትር በመላው ዓላም ተከባሪ ።
ጡትሽንሂ በሩቅ ያየ የቱርግ ገበሬ ፈካሪ
ደረትሽንም ያስተዋለ እንደ ፀሐይ ስታበሪ
አገባለሁ ብሎ ሲሮጥ አንች ወደሽው ባትዘሪ
ማጅራቱን ጠቀለለው ንጉሥሽ ባለሱሪ ።